ስግደት

1/ ስግደት!!!

ስግደት እንኳን እግዚአብሄር ለመረጣቸው ቅዱሳን ይቅርና 72 72 ለባለስልጣናት ፤በእድሜ ለሚበልጡን ና ለአዛውንቶች እራስን አዘንብሎ እጅ በመንሳት የሚደረግ የእክብሮት መግለጫ አለ።ከዚህ በታች ይህን የሚሳዩ ጥቅሶች እንመልከት

ያዕቆብም ዓይኑን አነሣ፥ እነሆም ዔሳውን ሲመጣ አየው፥ ከእርሱም ጋር አራት መቶ ሰዎች ነበሩ ልጆቹንም ከፍሎ ወደ ልያና ወደ ራሔል ወደ ሁለቱም ባሪያዎች አደረጋቸው

ባሪያዎችንና ልጆቻቸውንም በፊት አደረገ፥ ልያንና ልጆችዋንም በኋለኛው ስፍራ፥ ራሔልንና ዮሴፍንም ከሁሉ በኋላ አደረገ።

እርሱም በፊታቸው አለፈ ወደ ወንድሙም እስኪደርስ ድረስ ወደ ምድር ሰባት ጊዜ ሰገደ። ዘፍ 33፥1-3

ዳዊትም ጉባኤውን ሁሉ። አምላካችሁን እግዚአብሔርን ባርኩ አላቸው። ጉባኤውም ሁሉ የአባታቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ባረኩ፥ ራሳቸውንም አዘንብለው ለእግዚአብሔርና ለንጉሡ ሰገዱ።1 ዜና 29፥20-21

ይህ ከሆነ ስለ ጸጋ ስግደት መጸሃፍ ቅዱስ ምን ይላል??

በብሉይ

የአምሳ አለቃ ወጥቶ በኤልያስ ፊት በጉልበቱ ተንበረከከና። የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ነፍሴና የእነዚህ የአምሳው ባሪያዎችህ ነፍስ በፊትህ የከበረች ትሁን።2 ነገ 1፥13

የዚያን ጊዜም ንጉሡ ናቡከደነፆር በግምባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት። ዳን 2፥46

ነብዩ ኤልሳዕ የሱናማዊት ሴት ልጅ ካዳነ ቡኋላ . . . .ገብታም በእግሩ አጠገብ ወደቀች በምድርም ላይ ተደፋች ልጅዋንም አንሥታ ወጣች 2 ነገ 4፥37

ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር። ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ ፊቱንም ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ፥ዘፍ 19፥1

እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና። ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድር ነው? አለው።ኢያ 5፥14

ኢያሱ አምላኬ ብሎ እንዳልሰገደ ግልፅ ነው እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።ኢያ 24፥15 ብሎ የተናገረ ነቢይ ነውና

በሀዲስ

አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ያለው የእክብሮት ስግደት አሁን እንደቀጠለ ነው ነገር ግን አንድንዶች ከታች ያሉትን ሁለት ጥቅሶች ጠቅሰው ስግደት አይገባም ይላሉ ይህውም፡-

ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ። እርሱም፦ እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፥ራዕ 19፥10 ፤ራዕ 22፥9

ጴጥሮስም በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተገናኝቶ ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት። ጴጥሮስ ግን። ተነሣ፤ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ብሎ አስነሣው።ህዋ 10፥

25-26

በመሰረቱ እንግዲህ እርሱ ያከበራቸውን ማክብር እንጂ መናቅ ባለቤቱን መናቅ እንደሆነ ልብ ይለዋል እንጂ የእግዚአብሄር ወገን መሆንን አያሳይም በመፅሃፍ

አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።ሮሜ 8፥30 ተብሎ እንደተፃፈ ለቅዱሳን ክብር ይገባቿል።

ኢያሱ ሲሰግድ አዳታደርገው ተጠንቀቅ ያላለው መልአክ ዮሃንስን ለምን አለው?? ዮሃንስ በመንፈስ ቅዱስ የሚሚራ መሆኑን ተፅፏል (ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል።ዮሃ 16፥ 13) ታዲያ ቅዱስ መንፈስ ዮሃንስን ወደ ተሳሳተ መንገድ መራው?? ዮሃንስ ለማን መስገድ እንዳለበትስ አያወቅም??

ስለዚህ እነዚህ ሁለት ጥቅሶች የጸጋ ስግደት እንድንሰግድ የሚያስገነዝብ ነው ቅዱስ መንፈስ ወደ ተሳሳተ መንገድ ይመራል ካላልን በቀር ታዲያ የመልአኩ መልስ ስለ የትህትና ፤የዮሃስን ክብር ለመግለጥ(ዮሃንስ ቃል ስጋ ሆነ የሚለውን የፃፈ ነባቤ መለኮት የተሰኘ ታላቅ ነውና) ፤ስለ ዮሃንስ ስልጣነ ክህነት ሲል(1 ቆሮ 6፥2-3) እንደሆነ ልንረዳ ይገባል። ቅዱስ ጴጥሮስም እኔ እራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ማለቱ ስለ ትህትና እራስንም ዝቅ አድርጎ ለመታየት ሀዋሪያት ካለቸው ፍላጎት አንጂ በሰው ፊት የከበዱ እንደሆኑ አስቀድምው ተናግረዋል

የክርስቶስም ሐዋርያት እንደ መሆናችን ልንከብድባችሁ ስንችል፥ ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም።1 ተሰ 2፥6

ይህ እንዲህ ሲመለስላቸው ፣ ለወትሮው ለእግዚአብሄር የሚሰገደው በመንፈስ እንጂ በጉልበት አይደለም የሚሉ የስንፍና ዝናር የታጠቁ ፣ ለእግዚአብሄር ሰግደው የማያውቁ ቴሌቭዥናቸው እየመሰከረባቸው ግን ለማስመሰል ማቴ 4፥10 ጠቅሰው እንዲያውም ለአምላክህ # ብቻ ስገድ ይላል በማለት እኛን በከሰሱበት ክስ ወንጌላዊውን ዮሃንስን ፣ ኢያሱን ሊከሱ ለራሳቸው ይመች ይጽፋሉ የሚገርመው መጽሃፉ "ለአምላክህ ስገድ እርሱን ብቻ አምልክ" ይላል ፣ የሚመለከው እርሱ ብቻ መሆኑን ነው የተጻፈው እንጂ ለአምላክህ ብቻ ስገድ አይልም።

ስለዚህ ቅዱሳን የከበዱ ፤ተለይተው የተጠሩ ፤የከበሩ ፤የጸደቁ ፤የተቀደሱ ናቸው!!!ይህ በራሳቸውና በእኛ ዘንድ የታወቀ ነው ነገር ግን ክብርን ከሰው አልፈልጉም። ይህ ማለት መናቅን ፈልገዋል ማለት ግን አይደለም!!! እራሳቸውን ከፍ ከፍ አላደረጉምና በእኛ ዘንድ ግን ክብር ሊለገሳቸው ይገባል ምክንያቱም ይከብዱናላ።

ስለዚህ ቅዱሳን የእግዚአብሄር መንፈስ ያድረባቸዋልና (በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።ራዕ 7፥15) ስለዛ ክብር ስግደት ይገባቸዋል።

2/ ፀሎት*

ሰዉ ወደ እግዚአብሔር መቅረብና መነጋገር የሚችልበት የመጀመሪያ

መንፈሳዊ መንገድ ፀሎት ነው። አንድ ህፃን በእናቱ ማህፀን እያለ ከእናቱ ጋር የሚገናኘው በእትብት አማካኝነት ነው። ፀሎት ማለትም 1 ክርስቲያን ከፈጣሪዉ ጋር የሚገናኝበት መንፈሳዊ እትብት ማለት ነው።ፀሎት ሰዎችና እግዚአብሔር የሚገናኙበት ድልድይ ነው።ፀሎት ከውስጥ የሚመነጭ የልብ መቃተት ስለሆነ ቃላት ብቻ ሊገልፁት አቅም የላቸውም። በተመሰጠ ልብ፣ በመንፈሳዊ ሀሳብ፣ በተሰቀለ ህሊና ወደ አምላካችን የምንነጠቅበትና ከፈጣሪያችን ጋር የምንነጋገርበት ስለሆነ ፀሎት ከቃላት በላይ ነው። ፀሎት እግዚአብሔር እንዲያነፃን እንዲቀድሰን ልባችንን የምንከፍትበት የልብ ቁልፍ ነው።ፀሎት ክፉ ሀሳብ ከውስጣችን የሚወገድበት መንገድ ነው። ከጨለማ ኃይላት ርቆ ወደ መንፈሳዊ ህይወት መግባት የሚቻለው በፀሎት ነው። ፀሎት አጋንንት የሚፈሩትና የሚንቀጠቀጡበት መንፈሳዊ መሳሪያ ነው። ከወጥመዱ ያመለጠ ፀሎተኛን ዲያብሎስ ይፈራዋል።"ይህ ሰው በጸሎቱ ኃይል እያገኘ ነው።በመንፈሳዊ ህይወቱ እየጠነከረ ነው። ስለዚህ አሁን እኔን ሊዋጋኝ ይነሳል " እያለ ይርዳል ይንቀጠቀጣልም። ከእግዚአብሔር ጋር በፀሎት የሚፈጠረውንም ጥልቅ ግንኙነት እርሱ አስቀድሞ ያጣው ነውና ይቀናበታል ይመቀኘዋል። ስለዚህ ዲያብሎስ በሚችለው አቅም ሁሉ ፀሎትህን ለማስተው ይጥራል። ጊዜ እንደሌለህ እንደተጣበብክ ፣ እንደ ደከመህና እረፍት እንደሚያስፈልግህ እየነገረህ ፀሎትህን ለማስተው ይታገላል። በፀሎትህ ብርቱና የምትተጋ ብትሆንበትም ከመንገድ ለማሳት ሀሳብህን ለመበተን ሰይጣን የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም።ወዳጄ ሆይ ምንም ዉጊያው ፈታኝ ቢሆንብህም በሙሉ ሀሳብህ በፍፁም ልብህ በፀሎትህ በርታ! ፅና ! ሐዋሪያው እንዳለው ዲያብሎስን

ተቃወመው ከአንተም ይሸሻል።(ያዕ 4:7) ራሱ ጠላትህ እንደተናገረው ፀሎት የማይቋቋመው የማይችለው መሳሪያ ስለሆነ ሙሉ ትግሉ ሊያስቆምህ ነውና በፍፁም መንገድ አትስጠው፣ ተዋጋበት እንጂ ትጥቅህን አትፍታው።የቱንም ያህል ቢፈታተንህ የመንፈሳዊ ትግልህን ቁርጠኝነት አይቶ አፍሮ እንዲተውህ ፀልይ! ፀልይ ! እግዚአብሔርም በጸጋ አይለይህም። ስለዚህ ፀልዩ ። እኔን ደካማዉ ወንድማችሁንም በፀሎታችሁ አስቡኝ።

ፊሊሞን ታፈረ

ምንጭ፡ጉዞ ወደ እግዚአብሔር

3/ ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት በዝርዝር ሲገለጹ

፩. ነግኅ............. ፭. ሠርክ

፪. ሠለስት...........፮. ንዋም

፫. ቀትር ........... ፯. መንፈቀ ሌሊት ናቸው።

፬. ተሰዓት

"ስብዐ ለዕለትየ እሴብሐከ በእንተ ኩነኔ ጽድቅከ"( ስለ ጽድቅኽ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንኻለኊ) (መዝ ፻፲፰፥፻፷፬)

በነዚኽ ሰዓታት ይምንጸልይበት ምክንያት፦

=>ሀ/ ነግህ (ማለዳ ጧት)

ክቡር ዳዊት በመዝ ፭፥፫ ላይ "በማለዳ ድምፄን ትሰማለኽ በማለዳ በፊትኽ

እቆማለኍ" በማለት እንዳስተማረ ጽልመተ ሌሊትን አርቆ ብርሃነ መዓልትን ያመጣለንን አምላክ ማመስገን ተገቢ ነውና፤

- የኹላችን አባት አዳም የተፈጠረበት ሰዓት ማለዳ ነውና (ዘፍ ፩፥፳፯)

- ክብር ይግባውና አምላካችን ክርስቶስ በጲላጦስ ፊት ቁሞ የተመረመረበት ሰዓት ነውና (ማቴ ፳፯፥፩)

=>ለ/ ሠለስት (ሦስት ሰዓት)፦

- የኹላችን እናት ሔዋን የተፈጠረችበት ሰዓት ነው (ዘፍ ፪፥፳፩-፳፬)

- ነብዩ ዳንኤል የእልፍኙም መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አንጻር በመክፈት ጸሎት ያደረገበት ሰዓት ነው (ዳን ፮፥፲)

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት ሰምታ ጌታችንን የጸነሰችበት ሰዓት ነው (ሉቃ ፩፥፳፮)

- ክብር ይግባውና ጌታችን በጲላጦስ ፊት የተገረፈበት ሰዓት ነው (ማቴ ፳፯፥፳፮)

-በጽርሐ ጽዮን መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደበት ሰዓት ነው (የሐዋ ፪፥፲፭)

=>ሐ/ ቀትር (ስድስት ሰዓት)

- የፀሐይ ግለት የሚበረታበት ሰዓት ከመኾኑ አንጻር አእምሮ ሲዝል አጋንንት ይሰለጥናሉና እንዳይሰለጥኑብን (መዝ ፺፬፥፲፮፤ ፺፥፮)

- አዳም ዕፀ በለስን በልቶ የካደበት ሰዓት ነውና ከፈተና ለመጠበቅ (ዘፍ ፫፥፮)

- የአዳም ሰባተኛ ትውልድ የኾነው ሔኖክ ቤተ መቅደስን ያጠነበት ሰዓት ነው (ኩፋ ፭፥፴፪)

- ክብር ምስጋና ይግባውና ለዓለም ቤዛ ፈጣሪያችን መድኀኔ ዓለም በመስቀል ላይ የተሰቀለበት ሰዓት ነው (ዮሐ ፲፱፥፲፰)

=>መ/ ተስዓት (ዘጠኝ ሰዓት)

- ሊቃውንት እንደሚያስተምሩት መላእክት ሰው የጸለየውን ጸሎትና ምግባሩን የሚያሳርጉበት ሰዓት ነው (የሐዋ ፲፥፫)

- ቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ይወጡበት የነበረበት ሰዓት ነበርና (የሐዋ ፫፥፩)

- ክብር ይግባውና የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው የለየበት ሰዓት ነውና (ማር ፲፭፥፴፬-፴፯)

=>ሠ/ ሠርክ (ዐሥራ አንድ ሰዓት)

- ሠርክ የምጽአት ምሳሌ ሲኾን ይኸውም ሰው በዚኽ ዓለም ሥራውን ሲሰራ ውሎ ዋጋውን የሚቀበል በዐሥራ አንደኛው ሰዓት እንደኾነ ኹሉ ምእመናንም ምግባር ትሩፋት ሲሠሩ ኑረው ዋጋቸውን የሚያገኙት በምጽአት ነውና (ማቴ ፳፥፩-፲፮)

- ነብዩ ዳዊትም በመዝ ፻፵፥፪ ላይ "ጸሎቴን በፊትኽ እንደ ዕጣን ተቀበልልኝ፥ እጅ መንሣቴም እንደ ሠርክ መሥዋዕት ትኹን" በማለት ለጸሎት የተመረጠች ሰዓት መኾኗን ሲገልጽ፤ ነብየ እግዚአብሔር ኤልያስም በዚኽ ሰዓት የሠዋውን መሥዋዕትና ያቀረበውን ጸሎት ሲቀበልለት ዕዝራም ታላቅ ጸሎትን አቅርቦበታል (፫ነገ ፲፰፥፴፮፤ ዕዝ ፱፥፭)

- ክብር ይግባውና አምላካችን ዐማኑኤል ወደ ከርሠ መቃብር የወረደበት ሰዓት ነው (ማቴ ፳፯፥፶፯-፷፩)

=>ረ/ ንዋም (የመኝታ ሰዓት)

- የመዓልቱን ሥራ አሳልፎ ዕረፍተ ሌሊትን ያመጣኽልን አምላክ ተመስገን ተብሎ መጸለይ ስለሚገባ

- ክብር ይግባውና ጌታችን ለሐዋርያት በጌቴሴማኒ ሥርዐተ ጸሎትን ያስተማረበት ሰዓት ነውና (ማቴ ፳፮፥፴፮)

=>ሰ/ መንፈቀ ሌሊት

- ክብር ይግባውና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት፣ የተጠመቀበት፣ የተነሣበትና ዳግማኛም ይኽነን ዓለም ለማሳለፍ የሚመጣበት ሰዓት ነውና (ሉቃ ፪፥፯-፳፤ ፫፥፳፩፤ ዮሐ ፳፥፩፤ ማቴ ፳፰፥፩፤ ማር ፲፫፥፴፭)

- ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ በእሥር ቤት ውስጥ እያሉ በዜማ ልዑል እግዚአብሔርን ያመሰገኑበት ሰዓት ነው (የሐዋ ፲፮፥፳፭)

- ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በዚኽ በሰባቱ ጊዜያት በሚጸለየው የጸሎትና የሃይማኖት መጽሐፉ ውስጥ በስፋት ልዑል እግዚአብሔርን ሲያመሰግን ዳግምኛም በነዚኽ ሰዓታት ውስጥ ከተደረጉት ታሪኮች በመነሣት ብዙ ምስጢርንም አመስጥሮበታል።

ምንጭ፦ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ አስደናቂው የሰባቱ ጊዜያት የሃይማኖትና የጸሎት መጽሐፍ ንባብና ትርጓሜው

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

Miko ZE Ethiopia

4/ ስግደት- ለጌታ ብቻ

ወገኖቻችን በማስመሰል ማታለልን ይወዳሉና ክርስቶስን ያከበሩ ለማስመሰል ለእርሱ ብቻ ነው የሚሰገደው ይላሉ፤ ኦርቶዶክሶች ለጣዖት ነው የምትሰግዱት፤ አምልኮታችሁም ከእግዚአብሔር የራቀ ነው ይሉናል ለዚህም እነዚህን ማስረጃዎች ይጠቅሳሉ፦

(((ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ። ሉቃ. 4፥ 8)))

(((እኔ ህያው ነኝ ይላል ጌታ ጉልበትም ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል መላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ሮሜ. 14፥11)))

ይህንን ቃል ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትቃወማለችን??? በፍጹም አትቃወምም ቃሉ የታመነ ነው ነገር ግን ጥያቄው ብቻ የሚለው ከየት መጣ??? ቃሉስ የሚያወራው ስለ የትኛው ስግደት ነው??? ስግደት ሁሉ አምልኮ ነውን??? እናት ቤተክርስቲያናችን ይህን በደንብ ለይታና አጣርታ የመጽሐፉን ቃል ሳትቆራርጥ በበቂ ማስረጃ ታስተምራለች።

እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ እንስጥ ስለ ብርሃን ብንነጋገር ክርስቶስ እውነተኛ ብርሃን ነው፤ ብርሃንነት የባህሪው ነው፤ ብርሃንነትን ማንም ሊሰጠውም ሊነጥቀውም አይችልም ብለን እንገልጻለን

እንጂ ብርሃን ክርስቶስ ብቻ ነው አንልም እርሱ ራሱ እንዲህ ይለናልና፡-

(((እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። ማቴ. 5፡14)))

አስቀድሞ (((እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ። ዮሐ. 8፡12))) ያለን ጌታ መድኃኒዓለም መልሶ (((እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። ማቴ. 5፡14))) ይለናል። ስለዚህም የክርስቶስን ብርሃንነትና የእኛን ብርሃንነት ልዩነት መረዳት ይገባናል እንጂ ብቻ ብቻ ብቻ እያልን መሰረታዊውን ትምህርት ገደል ልንከተው አይገባም። ታዲያ እውነታው ምንድነው ብንል ከላይ እንደገለጽነው የክርስቶስ ብርሃንነት የባህሪው ሲሆን የእኛ ግን እርሱን በማመን የሚገኝ፤ ከእርሱ የሚሰጠን፤ እርሱ ሊወስድብንም የሚችል የጸጋ ብርሃንነት ነው። ስለ ስግደትም ስንነጋገር የአምልኮና የጸጋ ስግደትን ልዩነት ልንረዳ ይገባናል እንዲያ ካልሆነ ግን በመጽሐፍ ስለ ስግደት የተጻፉትን ሁሉ ከአምልኮ ጋር ካገናኘናቸው መጽሐፉን የጣዖት አምልኮ መጽሐፍ እናደርገዋለን።

ስግደት ለቅዱሳን፡-

(((የዚያን ጊዜም ንጉሡ ናቡከደነፆር በግምባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት። ዳን.2፡46)))

እግዚአብሔር ሞገስንና ምሕረትን የሰጠው ዳንኤል ሲሰገድለት ያልተቃወመው እንደ እግዚአብሔር መመለክ ፈልጎ ይሆን??? ራሱን ከአምላኩ ጋር ማስተካከልን ተመኝቶ ነውን???

(((ከኢያሪኮም መጥተው በአንጻሩ የነበሩት የነቢያት ልጆች ባዩት ጊዜ የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ዐርፎአል አሉ ሊገናኙትም መጥተው በፊቱ ወደ ምድር ተደፉ። 2ኛ ነገ. 2፥ 15)))

ነቢዩ ኤልሳ ልክ እንደ ዳንኤል ሲሰገድለት ዝም አለ መቼም ስላላወቀ ነው እንዳንለው ነቢይ ነውና እንኳን እየቀረበለት ስላለው ስግደት ወደ ፊት የሚሆነውን እንኳን ያውቃል።

ስግደት ለቅዱሳን መላእክት፦

(((ኢያሱ ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደ። ኢያ. 5፥14)))

መልአኩ ኢያሱን የሚያህል ታላቅ ሰው ሲሰገድለት እያየ ዝም አለ።

ለህሊናችሁ ካልከበዳችሁ አንድ እንጨምርላችሁ፦

(((ዳዊትም ጉባኤውን ሁሉ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ባርኩ አላቸው። ጉባኤውም ሁሉ የአባታቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ባረኩ ራሳቸውንም አዘንብለው ለእግዚአብሔርና ለንጉሡ ሰገዱ። 1ኛ ዜና 29፥20)))

እንግዲህ ምን እንላለን እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርና ቅዱስ ዳዊትን እኩል እያመለኩ ነውን??? ንጉሥ ዳዊትስ ሲሰግዱለት ለምን ዝም አለ??? በአምልኮቱ ቀናተኛ የሆነው እግዚአብሔርስ ሲሰገድለት ዝም የሚለውን እንደ ፕሮቴስታንቱ አገላለጽ ሲመለክ የማይቃወመውን ንጉሥ ዳዊትን እንዴት እንደ ልቤ ብሎ ጠራው??????

ይህ ሁሉ በብቻ አዚም መያዝ አይደለምን ስለዚህም

እንላችኋለን ከብቻ አዚም ተላቀቁ እውነትን ፈልጉ። እኛ

የተዋህዶ ልጆች ግን የአምልኮት ስግደትን ለእግዚአብሔር

እናቀርባለን ከእርሱም ሌላ የምናመልከው የለም፤ መጽሐፉ

እንዳስተማረን ደግሞ ለቅዱሳኑ የሚገባቸውን የጸጋ ስግደት

እናቀርባለን።

ኢያሱ ጣዖት አምላኪ ነው ካላችሁ፤ የኤልያስ መንፈስ እጥፍ

ሆኖ ያደረበት ነቢዩ ኤልሳ የክብሩን ልክ አያውቅም ካላችሁ፤

እግዚአብሔር ራሱ እንደ ልቤ ብሎ የመሰከረለት ቅዱስ ዳዊት

እንደ ሳጥናኤል አምልኮትን ለራሱ ፈልጓል ካላችሁ እኛንም

ከእነርሱ ጋር ደምሩን።

እግዚአብሔር አምላክ ከአዚም ያላቃችሁ፤ እኛንም

በእውነተኛይቱ መንገድ በተዋህዶ ያጽናን። አሜን!!! by@tekle

"የምናስተውል ካለን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል"፤

 በሚሞት ስጋችሁ ሐጢያት አይንገስ

ብልቶቻችሁን የፅድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ (ሮሜ 6፥12-14)

 ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው ካልተቻለ ዝሙትን ለመከላከል

በአንድ ይፅና ከዚህ ውጭ ጉዞ ወደ እሳት ነው (1ኛ ቆሮ 7፥1)

- ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱ ያፈርሰዋል ቤተ መቅደሱም እናንተው ናችሁ (1ኛ ቆሮ 3፥17)
- ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእረፍትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸፍኑ (1 ኛ ጢሞ 2፥9)
- የወንድ ልብስ የለበሰች ሴት በአምላክ ዘንድ የተጠላች ናት (ዘዳ 22፥5; ዘፀ 39፥28)
- ፀጉሯን ሳትሸፍን የምትፀልይ ሴት እራሷን ያዋረደች ናት(1ኛ ቆሮ 11፥5)
- የወይን ጠጅ ከሚጠጣ ጋር አትቀመጥ (ምሳ 23፥20)
- ዘፈን የሰነፎች ዜማ ነው (መክ 7፥5)
- በዛም አጋንንት ይዘፍናሉ (ኢሳ 13፥21)

Miko ZE Ethiopia

POSTED BY BINI ZELIDETA ‹‹

5/ ለቅዱሳን ስግደት ይገባል !!!(ተከታታይ ትምህርት ክፍል-27)

“ሳኦልም ሳሙኤል እንደሆነ አወቀ በፊቱም አጐነበሰ በምድርም ላይ እጅ ነሳ” 1ኛ ሣሙ.28÷14(ሳኦል ሳሙኤልን በማክበር መስገዱን ልብ በል)

“ከኢያሪኮም መጥተው በአንጻሩ የነበሩት የነቢያት ልጆች ባዩት ጊዜ የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ አርፎአል አሉ ሊገናኙትም መጥተው

(በፊቱ ወደ ምድር ተደፋ)" 2ኛ ነገ 2÷15። አያችሁ መንፈስ ቅዱስ ላደረባቸው በእግዚአብሔር ለተመረጡ ቅዱሳን አባቶች መስገድ ተገቢ መሆኑን አውቀው እንደሰገዱ?

"አብድዩም በመንገድ ሲሄድ እነሆ ኤልያስ ተገናኘው አብድዩም አውቆ (በግንባሩም ተደፍቶ) ጌታዬ ሆይ ኤልያስ አንተ ነህን? አለው" 1ኛ ነገ 19÷7::

"በዚያን ጊዜ ናቡከደነጾር በግንባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት" ዳን 2÷46።

"ጴጥሮስ በገባ ጊዜ ቆርኖሊዎስ ተገናኝቶ ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት" ሐዋ.ሥራ 10÷25::

<<<ለመላእክት ስግደት ይገባል !!!

"ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሎጥ ቤት መጡ ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሳ ፊቱን ደፍቶ (ወደ ምድር ሰገደ)" ዘፍ 19÷1-2።(ለመላእክት ስግደት የማይገባ ቢሆን ኖሮ ሎጥ ባልሰገደም ነበር)

"እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ የእግዚአብሔርን መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ (ሰገደም በግንባሩም ተደፋ)" ኦሪት ዘኍልቊ 22÷31።

"እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ አለ ኢያሱም ወደ ምድር በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድነው አለው" ኢያሱ 5÷13::

"ዳዊትም ዓይኖቹን አነሳ የእግዚአብሔርም መልአክ በምድርና በሰማይ

መካከል ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ሆና ወደ ኢየሩሳሌምም ተዘርግቶ አየ ዳዊትና ሽማግሌዎቹም ማቅ ለብሰው በግንባራቸው ተደፉ" 1ኛ ዜና መዋ 2÷16::

በተጨማሪም:-

- ዳንኤል ለቅዱስ ገብርኤል በኡባል ወንዝ መካከል ሰግዷል ዳንኤል 8÷15::
- ማኑኤና ሚስቱ ለመልአኩ ሰግደዋል መሳፍንት 13÷20::
- የዮሐንስ ራዕይ 19÷10 ላይ ዮሐንስ ለመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰግዷል። ነገር ግን መናፍቃን ዮሐንስ ለመልአኩ በሰገደ ጊዜ ለእኔ አትስገድልኝ ስላለው ለመላእክት ስግደት አይገባም በማለት ይናገራሉ:: በእርግጥም በዚህ ምዕራፍ ላይ መልአኩ ዮሐንስን እንዳትሰግድልኝ ብሎታል። ይህን ያለበት ምክንያት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ትህትናውን ለመግለፅ ሲሆን በሌላም በኩል የወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ክብር ከመላእክት እኩል ደርሶ ስለነበር ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው ዮሐንስ ከሐዋርያት ሁሉ የተለየ ክብር ነበረው ጌታም ይወደው የነበረው ሐዋርያ እርሱ ነበር ። አንድም ሞትን ባለመቅመሱ(በመሰወሩ) ምክንያት እንደ መላእክት አስቆጥሮታል። መላእክት አይሞቱምና (ዮሐንስም አልሞተም)። በተጨማሪም አንድ ቀን ጌታችን የደቀመዛሙርቱን እግር ለማጠብ ሲል የወገቡን መታጠቂያ(መቀነት) አውልቆ ባስቀመጠ ጊዜ ዮሐንስ አንስቶ ቢታጠቀው የሥጋ ፈቃዱ ሁሉ ጠፍቶለታል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዮሐንስ ኑሮው እና ክብሩ እንደ መላእክት ነበር። ስለዚህ መልአኩ አትስገድልኝ ያለው ይህን ክብሩን ያውቅ ስለነበር ነው። ከምንም በላይ ደግሞ ቅዱስ

ዮሐንስ የመጠቀ መለኮታዊ ዕውቀት የነበረው ሐዋርያእና ወንጌላዊ ነበር። ታዲያ ለመላእክት የማይሰግድ ቢሆን ኖሮ እንዴት ሊሰግድ ቻለ? እኛን በወንጌል ያነጸ ታላቅ አባት ሆኖ ሳለ እንዴት ለኛ የማይሆን ነገር ጻፈልን? ስግደት ለመላእክት የማይገባ ቢሆን ኖሮ ከዮሐንስ በላይ የሚያውቅ ሰው ነበርን? ደግሞም መልአኩ አትስገድስ ስላለው ዮሐንስ ከመስገድ ወደ ኋላ አላለም። በጣም የሚገርመው ነገር ቀድመን ባየነው ምዕራፍ ላይ ዮሐንስ ተሳስቶ ሰገደ ብንል እንኳ ራዕይ 22÷8 ላይ ዮሐንስ በድጋሚ ለመልአኩ ሰግዷል። (ታዲያ ዮሐንስ በድጋሚ መስገዱ ተሳስቶ ይሆን? )እኛ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እንድንጠብቅ የነገረንና በወንጌል ያነጸን ታላቅ መምህር ሆኖ ሳለ የማይሆን ነገር አደረገ ልንል ይሆን?

+++ በመሠረቱ ለቅዱሳን መስገድ እና አለመስገድ የትህትና እና የተዕቢት ጉዳይ ነው። ስግደት የትህትና መገለጫ ነው!!! አለመስገድ ይቻላል ነገር ግን ትዕቢት ነው!!! ስለዚህ ትሁት የሆነና ለቅዱሳን አክብሮት ያለው ይሰግዳል ፤ ልቡን በትዕቢት የሞላ ግን አይሰግድም !!! ስለዚህ ለቅዱሳን የመስገድ ጉዳይ የትህትና ጉዳይ ነው። ለምሳሌ ሰይጣን ከክብሩ የተዋረደው በትዕቢቱ ነው ይህም ለፈጠረው አምላክ አልሰግድም አልገዛም በማለቱ። የቀሩት ዘጠና ዘጠኙ የመላእክት ነገዶች ግን በትህትና ለአምላካቸው ሰግደዋል ፣ ተገዝተዋል እና እኛ የእነርሱን ፈለግ በመከተል ለፈጣሪያችን የአምልኮት ፣ ላከበራቸው ቅዱሳን ደግሞ የአክብሮት እና የጸጋ ስግደት እናቀርባለን ። መናፍቃን ደግሞ የግብር አባታቸው ዲያቢሎስ ነውና እንደርሱ በትዕቢት ተኮፍሰው ፣ ትህትናን ተነፍገው ለቅዱሳንም ሆነ ለጌታቸው ስግደትን አያቀርቡም !!!

+++የስግደት ዓይነቶች

1ኛ. የአምልኮ ስግደት፦ ይህ ስግደት የሚቀርበው ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህም ፈጥረኸናል ፣ ትገዛናለህ ፣ ታኖረናለህ ፣ ትመግበናለህ ስንል ለባሕርይ አምላክነቱ እንሰግድለታለን።

2ኛ. የጸጋ ስግደት፦ ይህ ስግደት ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የሚቀርብ ስግደት ነው። አምላክን ለመውለድ በተሰጣት ጸጋ በፍጹም ልባችን ለአምላክ እናት ለእመብርሃን እንሰግዳለን።

3ኛ. የአክብሮት ስግደት፦ ይህ ስግደት የሚቀርበው ለቅዱሳን፣ ለቤተክርስቲያን እና ለቅዱስ መስቀል ነው ። አምላክ መርጧችኋል ፣ አክብራችኋል ስንል እንሰግድላቸዋለን። ነገር ግን ያልታደሉ ሰዎች(መናፍቃን)ከተቃውሞ በቀር ፍሬ የላቸውምና ለእመቤታችንና ለቅዱሳን የምንሰግደው ስግደት ይቃወማሉ። እንደው ለተቃውሞ እንጂ አንድ ቀን እንኳ ለአምላካቸው ሲሰግዱ አይታችሁ ታውቃላችሁ??? ከሰገዱስ መቼ ፣ የት ??? ይቀጥላል (ይቆየን)።

Like . Liul Nunush

እራይ ምራፍ 19:9-10 እርሡ ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብጹፃን ናቸው ብለህ ጻፍ አለኝ ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋው ::እርሱም እዳታረገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ::

Like . Miko ZE Ethiopia

ለወንድሜ ማርቆስ ወልደ አማኑኤል . ራዕይ 19 ÷9-10 ለጠቀስከው

ጥቅስ ጸሁፋን ደግመህ ሙሉውን አንብበው ከላይ ብቻ አታንብብ። እንዲሁም በጸሁፉ ውስጥ የተጠቀሱትን እውነታዎች ለምን ዘለልካቸው? እነዚህ ማስረጃዎች ያሉት በእጅህ ይዘህ በትዞረው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ንባብ ይገላል ትርጓሜ ግን ያድናል።

Like · Miko ZE Ethiopia

ለወንድሜ ማርቆስ ወልደ አማኑኤል . .....በጣም የሚገርመው ነገር ቀድመን ባየነው ምዕራፍ ላይ ዮሐንስ ተሳስቶ ሰገደ ብንል እንኳ ራዕይ 22÷8 ላይ ዮሐንስ በድጋሚ ለመልአኩ ሰግዷል። (ታዲያ ዮሐንስ በድጋሚ መስገዱ ተሳስቶ ይሆን? )እኛ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እንድንጠብቅ የነገረንና በወንጌል ያነጸን ታላቅ መምህር ሆኖ ሳለ የማይሆን ነገር አደረገ ልንል ይሆን? ወንጌሉም እንዲህ ይላል የዮሐንስ፡ራእይ፥ምዕራፍ፡ 22÷8 ,,,,,,ይህንም፡ያየኹት

ና፡የሰማኹት፡እኔ፡ዮሐንስ፡ነኝ።በሰማኹትና፡ባየኹትም፡ጊዜ፡ይህን፡ባሳየኝ፡

በመልአኩ፡እግር፡ፊት፡እሰግድ፡ዘንድ፡ተደፋኹ።

Like . Dan Get

segedete egziabhare amelake kmimlkebachew mengdoch andu nw...seyetan kesmaye wede meder yettalew alsegdem bmaletu sayehon legziabhere yekrbe yenbrewen amelko lerasu bmmgnetu nw...selzi seytan lay yetwsdew ermja amleko segedte wedasa elelta hulu yemigbaw

bechgawe amlake egziabehare becha endhone yemiyasay new....

Like . Liul Nunush

አተ አምላክ ከላከው መላክ ለመብለጥ አትሞክር እሺ አስበህም ከሆ ተሳስተሀል ከፈለክ ደሙ ሌላ ልጨምርልህ እራይ 22-8,9 መልስየሚሰጥ የሌለ እዳይመስልህ ጌታ ለሁሉም መፈሱን ሰጥታል መጠቀ አለመጠቀም የሰውፋንታነው ዮሐንስ ለመላኩ የት ነው የሰገደው መልሰህ አብበው ይህን ምስኪን ሕዝብ አታታሉት ሐዋርያ ሥ 10፥25 ጴጥሮስ ያለው እኔራሴ ደግሞ ሰውነኝብሎ አስነሳው እንጂ ልክነህ አለው እደው የዚህ አይነት ነገር በአዲስ ኪዳን አለ

Like . Miko ZE Ethiopia

2 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 3፥6

<<እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል>>

Zewdnesh Mesfin .

6/ ለቅዱሳን በመስገዳችን እኛ አልተሳሳትንም!!!

ስግደት ለእግዚአብሔር ስግደት ለቅዱሳን

(ስግደትን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች ጠቅለል ያለ ግንዛቤንና ምላሽን ለመስጠት ያህል)

ክፍል 1

በፍጹም ልብ በፍጹም ነፍስ በፍጹም ኃይል (ዘዳ.6፥5) የሚወደድ የሆነውን አምላካችን እግዚአብሔርን ስናመልከው ሥጋችንንም፣ ነፍሳችንንም፣ መንፈሳችንንም አስተባብረን መሆን አለበት። መጻሕፍትን በማንበብ፣ ለብዎትን /ማስተዋልን/ በመጠቀም፣ ዕውቀትን ገንዘብ በማድረግ፣ ነቢብን /ንግግርን/ በማስገዛት፣ ህልዎትን / መኖርን/ በመሠዋትና በመሳሰሉት እግዚአብሔርን ማምለክ ባሕርያተ ነፍስን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ማስገዛት ነው። ጾም/ከሥጋ ፍላጎት መከልከል/ እና ስግደትን የመሳሰሉት ደግሞ በሥጋ እግዚአብሔርን የምናመልክባቸው፣ ሥጋችንን የምናስገዛባቸው መንገዶች ናቸው። ፍቅር፣ ቸርነት፣ ምኅረት፣ መመጽወት እና የመሳሰሉት የመንፈስ ሥራዎች ደግሞ ወደ ፍጹምነት የሚወስዱን የሥጋን ድካምና የነፍስን ሐልዮት የምንቀድስባቸው እንዲሁም መንፈሳችንን ለአምልኮተ እግዚአብሔር የምናስገዛባቸው መንገዶች ናቸው። ስለዚህ ስግደት የሰው ልጅ የተፈጠረበትን ዓላማ (የሰው ልጅ የተፈጠረበት ዓላማ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው) ከሚያሳካባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በሌላ አነጋገር

የሰው ልጅ ካለስግደት ሥጋውን ፍጹም መኮነን(መግዛት) አይችልምና ሰብእናው ምሉዕ አይሆንም።

ስግደት ስንት ዐይነት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ከአፈጻጸም ሥርዐት አንፃር ስግደት በሦስት ይከፈላል። የመጀመሪያው የስግደት አፈጻጸም ሥርዐት መሬት ላይ በመውደቅ ወይም ሙሉ በሙሉ ተደፍተው የሚሰግዱት ስግደት ሲሆን በልዩ ስሙ ወዲቅ በመባል ይታወቃል። "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት" የሚለው በሊቃውንት የተዘጋጀው የቤተክርስቲያናችን መጽሐፍ ይህንን የስግደት ዐይነት ሰጊድ /Prostration/ ብሎ ገልጾታል።(ገጽ 85) ዮሐንስ ወንጌላዊ "ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ።"/ራእ.19፥10/ ያለው ወዲቅን እንደተገበረ የሚያሳይ ነው። መደፋቱ ከድንጋጤ ወይም ከመፍራት ወይም ከመታመም የመጣ እንዳልሆነ ሲነግረን "ልሰግድለትም" አለ። በእግሩ ፊት የተደፋው ሊሰግድለት መሆኑን አስረዳ። ከዚህ በተጨማሪ "ፊቱንም ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ" /ዘፍ.19፥1/ "ሰገደም በግንባሩም ተደፋ" /ዘኁ.22፥31/ "በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደ" /ኢያ.5፥13/ "ማቅ ለብሰው በግንባራቸው ተደፉ" /1ኛ ዜና.21፥16/ "በፊቱ ወደ ምድር

ተደፉ" /2ኛ ነገ. 2፥15/ "በእግሩ አጠገብ ወደቀች፤ በምድርም ላይ ተደፋች" /2ኛ ነገ.4፥8/ "ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት" /ሐዋ.10፥25/ የሚሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ወዲቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የስግደት ዐይነት መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው።

ሁለተኛው የስግደት ዐይነት አስተብርኮ /Kneeling/ በመባል ይታወቃል። ይህም ስያሜው እንደሚጠቁመው ጉልበትን ሸብረክ በማድረግ፣ በጉልበት በመቆም ወይም በመንበርከክ የሚፈጸም ነው። ወዶ ፈቅዶ ራሱን ዝቅ አድርጎ በድኅነት ከፍ ላደረገን ክርስቶስ የአምልኮ ስግደትን መስገድ እንዲገባ ሲያጠይቅ "በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ... ነው" በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ፊሊጲስዩስ በላከው መልእክቱ የአስተብርኮ ስግደትን ለክርስቶስ መስገድ እንደሚገባ አስረድቷል። /ፊል. 2፥10/ ምንም እንኳን እያሾፉ ቢሆንም በማር. 15፥19 ላይ አይሁድ ለስም አጠራሩ ክብር ይሁንና ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ "ተንበርክከውም ሰገዱለት" ይላል። ምንም እንኳን ስግደታቸው የሹፈት፣ የማላገጥ ቢሆንም ጥቅሱ በመንበርከክ መስገድ እንዳለ የሚጠቁመን ነው። በዚሁ ምእራፍ በማላገጥ እጅ ነሥተውት ነበርና እጅ መንሣታቸው የሹፈት እንደሆነው

ሁሉ ስግደታቸውም የማሾፍ ነበር። እጅ በመንሣት አሹፈዋልና እጅ አይነሣም እንደማይባለው በመንበርከክ ሰግደዋልና በመንበርከክ መስገድ አይገባም አይባልም። አንዳንድ ሰዎች ተንበርክኮ መጸለይ፣ ተንበርክኮ መስገድ የእኛ ትውፊት አይደለም፤ የቤተክርስቲያን ሥርዐት አይደለም ብለው እንደሚያስተምሩና ተንበርክከው የሚጸልዩትንም እንደሚገሥጹ ጠቅሰው በዚህም የተነሣ ተንበርክኮ መጸለይንና በመንበርከክ መስገድን እንደሚፈሩ ብዙዎች ይናገራሉ። ሆኖም ተግሣጹ ስሕተት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ሌሎች ያዙትና መጽሐፍ ቅዱስን መያዝ የኛ አይደለም እንደማለት አይነት ከንቱ ጨዋነት ነው። ሌሎች ደጋግመው ጌታ ጌታ ይላሉና ጌታ ማለት የኛ አይደለም

እንደማለት ያለ አላዋቂነት ነው።

ሦስተኛው የስግደት አፈጻጸም ዐይነት አድንኖ /Bowing/ ይባላል። አድንኖ ራሥን፣ ግንባርን፣ አንገትን ዝቅ በማድረግ የሚሰገድ ነው - "አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ..." እንዲባል በቅዳሴ። ይህም እንደቀደሙት ሁለቱ የስግደት አፈጻጸም ዐይነቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ነው። በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 49 ቁጥር 23 ላይ "ግንባራቸውን ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል" ይላል። ካህናትም "በንስሐ

ውስጥ ያላችሁ ራሣችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ" ማለታቸው አድንኖን በመፈጸም ስገዱ ሲሉን ነው።

ወዲቅም፣ አስተብርኮም ሆነ አድንኖ የስግደት አፈጻጸም ዐይነቶች ናቸው እንጂ ከስግደቱ ዓላማ ጋር ወይም ከሚሰገድለት አካል አንጻር የሚፈጸሙ አይደለም። በሌላ አገላለፅ ሦስቱን የስግደት ዐይነቶች ስግደት ለሚገባው ሁሉ እንፈጽማለን - ሦስቱንም ዐይነት ስግደት ለእግዚአብሔርም ለቅዱሳንም እናቀርባለን። ነገር ግን የመስገዳችን ምሥጢሩ ይለያያል። ይህንንም እንደሚከተለው እንየው።

ስንዱዋ እመቤት ቅድስት ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ ከዓላማው አንፃር ሁለት ዐይነት ስግደት እንዳለ ታስተምራለች። በሌላ አገላለጽ ስግደቱ ከሚቀርብለት አካል ማንነት አንጻር ስግደት በሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያው ለእግዚአብሔር የምንሰግደው የስግደት ዐይነት ሲሆን የአምልኮ /የባሕርይ/ ስግደት ይባላል። /የአምልኮ ስንል በባሕርዩ አምላክ ለሆነው ማለታችን ነው፤ በጸጋ አማልክት የተባሉ እንደ ሙሴ ያሉ ቅዱሳን አሉና - ዘጸ.7፥1/ ይህን ስግደት አንድ አምላክ ከሚሆን ከእግዚአብሔር ውጭ ለማንም መስገድ አይቻልም። በዘወትር ጸሎት ላይ "እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐተ ስግደተ - ለአብ ለወልድ ለመንፈስ

ቅዱስ አንዲት ስግደትን እሰግዳለሁ” ማለቱ ይህንን ምሥጢር የሚገልፅ ነው። “አሐተ - አንዲት” የሚለው የስግደቱን መጠን ወይም ቁጥርን ለመግለፅ ሳይሆን ስግደቱ በባሕርዩ ለሚመለክ ለአንድ አምላክ የሚሰገድ ፣ ለሌላ አካል የማይሰገድ የአምልኮ ስግደት መሆኑን ሲጠቁመን ነው። “አንድ ጊዜ ብቻ ስገዱ” ብሎ ቁጥርን ለማመልከት ቢሆን ዝቅ ብሎ “3 ጊዜ በል” ብሎ አንዲት ስግደት የሚለውን 3 ጊዜ እያልን ሦስት ጊዜ እንድንሰግድ አያዘንም ነበር። “አንዲት” የሚለውን ቃል እንዲህ መተርጎማችን የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነትን ይዘን ነው። ብሥራተ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ሊያበሥር መላኩን ቅዱስ ሉቃስ ሲገልጽ “ወደ አንዲት ድንግል ተላከ” /ሉቃ.1፥27/ ብሏል። “አንዲት ድንግል” የሚለው ቁጥርን ሳይሆን የድንግሊቱን ልዩ መሆን የሚጠቁም መሆኑ ግልፅ ነው። እሷም ድንግልናዋ የተለዩ መሆናቸውን የሚገልፅ ነው። ቁትርን የሚገልፅ ነው ከተባለማ በዚያን ጊዜ በምድር ላይ አንዲት ድንግል ብቻ አለች ወይም በዚያን ጊዜ በምድር ላይ ያሉ ድንግሎች ብዛት ሁለት እንኳን አይሞላም ወደ ሚል ስሌት ይመራናል። ዕለቱን እንኳን ሺ የሚወለዱ ሕፃናት ደናግላን አሉ። በተመሳሳይም በዮሐንስ ራእይ “አንዲት ሴት ነበረች” /ራእ.12፥1/ ሲል በምድር ያሉት ሴቶች

ሁለት እንኳን አይሞሉም ለማለት ሳይሆን የሴቲቱን ፍጹም የተለየች መሆን፣ ወይም በእሷ ደረጃ የሚገኝ ሌላ ሴት/ ፍጡር አለመኖሩን ሲገልፅልን ነው። ብዙ ሴቶች በምድር እንደነበሩማ መጽሐፍ ቅዱሳችን በብዙ ቦታ መስክሯል። በተመሳሳይም ከላይ ጸሎተ ሃይማኖታችንም

አንዲት ስግደት ማለቱ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባ መሆኑን ሲያመለክት ነው።

ሁለተኛው ጸጋ እግዚአብሔርን ላገኙ ቅዱሳን ሁሉ የሚሰገድ የጸጋ ስግደት ነው። ቅድስት ድንግል ማርያም ፣ ቅዱስ መስቀል ፣ ቅዱሳን መላእክት ፣ ሰማዕታት ፣ ፃድቃን ፣ ቅዱሳን ፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፣ ቅዱሳን ቦታዎች ፣ ታቦት ፣ ቅዱሳት ንዋያት እዚህ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። የዘወትር ጸሎት "ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አንዲት ስግደትን እሰግዳለሁ" ብሎ አያቆምም፤ "አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ለድንግል ማርያምም እሰግዳለሁ፤ ዓለምን ሁሉ ለማዳን ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ ለተሰቀለበት መስቀልም እሰግዳለሁ" በማለት የጸጋ ስግደትን ለቅድስት ሥላሴ ከሚሰገደው የባሕርይ ስግደት ለይቶ እግዚአብሔር ለቀደሳቸው እንደሚገባ የሚያስረዳ ነው። እኛ የዘወትር ጸሎት የሚባል ነገር አናውቅም... የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አምጡ የሚሉም

ካሉ እንደሚከተለው እናስረዳለን።

“ሳኦልም ሳሙኤል እንደሆነ አወቀ በፊቱም አጐነበሰ በምድርም ላይ እጅ ነሳ” 1ኛ ሣሙ.28÷14(ሳኦል ሳሙኤልን በማክበር መስገዱን ልብ በል) “ከኢያሪኮም መጥተው በአንጻሩ የነበሩት የነቢያት ልጆች ባዩት ጊዜ የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ አርፎአል አሉ ሊገናኙትም መጥተው (በፊቱ ወደ ምድር ተደፉ)” 2ኛ ነገ 2÷15። አያችሁ መንፈስ ቅዱስ ላደረባቸው በእግዚአብሔር ለተመረጡ ቅዱሳን አባቶች መስገድ ተገቢ መሆኑን አውቀው እንደሰገዱ? “አብድዩም በመንገድ ሲሄድ እነሆ ኤልያስ ተገናኘው አብድዩም አውቆ (በግንባሩም ተደፍቶ) ጌታዬ ሆይ ኤልያስ አንተ ነህን? አለው” 1ኛ ነገ 19÷7:: “በዚያን ጊዜ ናቡከደነጾር በግንባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት” ዳን 2÷46። “ጴጥሮስ በገባ ጊዜ ቆርኖሊዎስ ተገናኝቶ ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት” ሐዋ.ሥራ 10÷25:: <<<ለመላእክት ስግደት ይገባል !!! “ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሎጥ ቤት መጡ ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሳ ፊቱን ደፍቶ (ወደ ምድር ሰገደ)” ዘፍ 19÷1-2። (ለመላእክት ስግደት የማይገባ ቢሆን ኖሮ ሎጥ ባልሰገደም ነበር) “እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ የእግዚአብሔርን መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ (ሰገደም በግንባሩም

ተደፋ)" ኦሪት ዘኍልቍ 22÷31። "እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ አለ ኢያሱም ወደ ምድር በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድነው አለው" ኢያሱ 5÷13:: "ዳዊትም ዓይኖቹን አነሳ የእግዚአብሔርም መልአክ በምድርና በሰማይ መካከል ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ሆና ወደ ኢየሩሳሌምም ተዘርግቶ አየ ዳዊትና ሽማግሌዎቹም ማቅ ለብሰው በግንባራቸው ተደፉ" 1ኛ ዜና መዋ 2÷16:: በተጨማሪም:- • ዳንኤል ለቅዱስ ገብርኤል በኡባል ወንዝ መካከል ሰግዷል ዳንኤል 8÷15:: • ማኑኤና ሚስቱ ለመልአኩ ሰግደዋል መሳፍንት 13÷20:: • የዮሐንስ ራዕይ 19÷10 ላይ ዮሐንስ ለመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰግዷል። ነገር ግን መናፍቃን ዮሐንስ ለመልአኩ በሰገደ ጊዜ ለእኔ አትስገድልኝ ስላለው ለመላእክት ስግደት አይገባም በማለት ይናገራሉ:: በእርግጥም በዚህ ምዕራፍ ላይ መልአኩ ዮሐንስን እንዳትሰግድልኝ ብሎታል። ይህን ያለበት ምክንያት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ትህትናውን ለመግለፅ ሲሆን በሌላም በኩል የወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ክብር ከመላእክት እኩል ደርሶ ስለነበር ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው ዮሐንስ ከሐዋርያት ሁሉ የተለየ ክብር ነበረው ጌታም ይወደው የነበረው ሐዋርያ እርሱ ነበር ። አንድም ሞትን ባለመቅመሱ(በመሰወሩ)

ምክንያት እንደ መላእክት አስቆጥሮታል። መላእክት አይሞቱምና (ዮሐንስም አልሞተም)። በተጨማሪም አንድ ቀን ጌታችን የደቀመዛሙርቱን እግር ለማጠብ ሲል የወገቡን መታጠቂያ(መቀነት) አውልቆ ባስቀመጠ ጊዜ ዮሐንስ አንስቶ ቢታጠቀው የሥጋ ፈቃዱ ሁሉ ጠፍቶለታል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዮሐንስ ኑሮው እና ክብሩ እንደ መላእክት ነበር። ስለዚህ መልአኩ አትስገድልኝ ያለው ይህን ክብሩን ያውቅ ስለነበር ነው። ከምንም በላይ ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ የመጠቀ መለኮታዊ ዕውቀት የነበረው ሐዋርያእና ወንጌላዊ ነበር። ታዲያ ለመላእክት የማይሰግድ ቢሆን ኖሮ እንዴት ሊሰግድ ቻለ? እኛን በወንጌል ያነጸ ታላቅ አባት ሆኖ ሳለ እንዴት ለኛ የማይሆን ነገር ጻፈልን? ስግደት ለመላእክት የማይገባ ቢሆን ኖሮ ከዮሐንስ በላይ የሚያውቅ ሰው ነበርን? ደግሞም መልአኩ አትስገድስ ስላለው ዮሐንስ ከመስገድ ወደ ኋላ አላለም። በጣም የሚገርመው ነገር ቀድመን ባየነው ምዕራፍ ላይ ዮሐንስ ተሳስቶ ሰገደ ብንል እንኳ ራዕይ 22÷8 ላይ ዮሐንስ በድጋሚ ለመልአኩ ሰግዷል። (ታዲያ ዮሐንስ በድጋሚ መስገዱ ተሳስቶ ይሆን? )እኛ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እንድንጠብቅ የነገረንና በወንጌል ያነጸን ታላቅ መምህር ሆኖ ሳለ የማይሆን ነገር አደረገ ልንል ይሆን? ይቅር የይበለን

ለቅዱሳንመስገድን ያስተማረው እግዚአብሔር ነው።
መጽሐፍ ቅዱስ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ ለቅዱሳን
መስገድ እንደሚገባ ያስረዳል። በዘፍ. 27፥29 "አሕዛብ
ይገዙልህ ሕዝብም ይስገዱልህ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን፥
የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ የሚረግምህ እርሱ ርጉም
ይሁን የሚባርክህም ቡሩክ ይሁን።" ብሎ ልጁን ያዕቆብን
የባረከው ይሥሐቅ ነበር። ይህን ምርቃት ማግኘት
የነበረበት የያዕቆብ ታላቅና በኩር የነበረው
ኤሳው ቢሆንም ያዕቆብ በእናቱ ብልኃት ታግዞ ተመረቀ።
ይሥሐቅን እንዲህ ብሎ እንዲመርቅ ያደረገው
እግዚአብሔር አምላክም የአብርሃም ፣ የይሥሐቅና
የኤሳው አምላክ በመባል ፋንታ የአብርሃም ፣ የይሥሐቅና
የያዕቆብ አምላክ ተባለ። አምላካችንን ሙሴ ማነህ ብሎ
በጠየቀው ጊዜም ራሱን ሲገልፅ እርሱ ራሱን ለአብርሃም
ለይሥሐቅና ለያዕቆብ የሚገለጥና ምድረ ርስትንም
ሊሰጣቸው ቃል እንደገባ ለሙሴ ገልፆለታል። ስለዚህ
በይሥሐቅ አንደበት አድሮ ያዕቆብን የመረቀው
እግዚአብሔር ነው። ይህንን የሚጠራጠሩ ቢኖሩ እንኳን
የይሥሐቅን ምርቃት የፈጸመው /እንዲደርስ ያደረገው/
እግዚአብሔር ነው። ታዲያ አምላካችን ለቅዱሳን የሚገባን
ስግደት የሚቃወም ቢሆን ይሥሐቅን "ሕዝብም
ይስገዱልህ" ብሎ ሲመርቅ አይገሥጸውም ነበርን?

ባይገሥጸው እንኳን “ልጆች ይሰገዱልህ” ብሎ የመረቀ ይሥሐቅን ምርቃቱን ባለመፈጸም /እንዲደርስ ባለማድረግ/ ቃሉ ልክ እንዳልሆነ አያሳይም ነበርን? ደግሞስ ለፍጡር በሚገባ መስገድ ስሕተት ቢሆን ከብዙ ዘመን በኋላ ያዕቆብ ከነቤተሰቡ ለኤሳው በመስገድ የአባቱን የይሥሐቅን “ስሕተት” ይደግመው ነበርን?

ከዘፍ.37-41 ድረስ የፃድቁን የዮሴፍን ታሪክ እናገኛለን። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ለዮሴፍ እንደሚሰገድለት የሚተነብይ ሕልም አሳየው። “እኔ ያለምሑትን ሕልም ስሙ፥ እነሆ እኛ በእርሻ መካከል ነዶ ስናሥር ነበርና፤ እነሆም የእኔ ነዶም ቀጥ ብላ ቆመች፤ የእናንተም ነዶች በዙሪያ ከበው እነሆ ለኔ ነዶ ሰገዱ” /ዘፍ.37፥7/። ወንድሞቹ ከሕልሙ የተነሣ እንደሚሰግዱለት ተረድተው ወንድማቸው ዮሴፍን ይበልጥ ጠሉት። ለቅዱሳን አንሰግድም ብለው ቅዱሳንን የማያከብሩ ሰዎች በትዕቢት ራሳቸውን ከቅዱሳን በላይ በማድረግ፣ ወንድማቸውን ዝቅ ያደረጉትን የዮሴፍን ወንድሞች ይመስላሉ። እግዚአብሔር ግን ይህንን እንዲረዱት ዮሴፍ ነዶ በተባሉት በወንድሞቹ ብቻ ተሰግዶለት የሚቀር ሳይሆን በሌሎች ፍጥረታትም ዘንድ እንደሚከብር ሲገልፅላቸው ዮሴፍን ሌላ ሕልም ዐሳየው። “እነሆ ደግሞ

ሌላ ሕልምን አለምሁ፣ እነሆ ፀሐይና ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ ዐየሁ" /ዘፍ.37፥9/። እግዚአብሔር ተናግሮ ነገር አይቀርምና ወንድሞቹ እንዳይሰግዱለት፣ እንዳይገዙለት ሽተው ሊገድሉት ቢሞክሩም፣ ጉድጓድ ውስጥ ቢጥሉትም፣ ለነጋድያን ቢሸጡትም በሀገራቸው ሊፈጽሙት የከበዳቸውን ሐቅ ርሐብና ድርቅ ሲመጣ በባዕድ ምድር በግብፅ ሊያደርጉት ግድ ሆኖ ወንድሞቹ ለዮሴፍ መስገዳቸው አልቀረም። "የዮሴፍም ወንድሞች በመጡ ጊዜ በግምባራቸው በምድር ላይ ሰገዱለት" /ዘፍ.42፥6/። ለቅዱሳን አንሰግድም የሚሉ ሰዎች ምንም እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ሊያጠፉት ሽተው ቢሰርዙና ቢደልዙትም፣ በቀላል አማርኛ በሚል ፈሊጥ ቃሉን ቢዘነጥሉትም፣ ጥቅስን ዘንጥሎ በመጣል ጉድጓድ ውስጥ ቢጥሉትም፣ አውጥተው ለሥጋዊ ስሜትና ለዓለም ክህደት ቢሸጡትም ርሐበ ነፍስ ድርቀተ መንፈስ ሲመጣ በሀገራቸው፣ በሕይወተ ሥጋቸው ያላደረጉትን እውነትን በሲዖል እንኳን ለማድረግ መጓጓታቸው አይቀርም። "የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ" እንዳለ ኢሳይያስ /ኢሳ.60፥14/። በምድር ምጽዋት የነፈገውን አልአዛርን በሲዖል በአብርሃም አማላጅነት እንደለመነው ነዌ። /ሉቃ.16፥20-31/።

ጳዎሎስንና ሲላስን ለመሰሉ ቅዱሳን ለእናንተ የሚገባው ስግደት ሳይሆን መታሠር ነው ብለው ደብድበው ካሠሯቸው ሰዎች መኃል አንዱ የሆነው የእሥር ቤቱ ጠባቂ በእሥር ቤቱ ውስጥ በነጳውሎስ ዝማሬ ምክንያት ከደረሰው ታላቅ መናወጽ በኋላ ከሥራቸው ተደፍቶ ሰገደላቸው። "ከጳውሎስና ከሲላስ ፊት ተደፋ" /ሐዋ.16፥ 29/ እንዲል ግብረ ሐዋርያት። የቅዱሳኑን ዝማሬ ሰምቶ እሥር ቤቱን አናውጾ ጠባቂውን እንዲሰግድ ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን? እግዚአብሔር ቃል በቃል ለቅዱሳን ስግደት እንደሚገባ የተናገረበት ቦታን ለሚሻ ደግሞ እነሆ፦

በራእየ ዮሐንስ ምዕራፍ ሦስት ላይ ሁለት የቤተክርስቲያን ጠባቂዎችን እናገኛለን። አንደኛው በሰርዴስ የሚገኘው መልአክ /ጠባቂ/ ሲሆን አንደኛው ደግሞ የፊልድልፍያ ቤተክርስቲያን መልአክ /ጠባቂ/ ነው። የሰርዴሱ ጠባቂ ሥራው በአምላክ ፊት ፍጹም ያልሆነና በቁሙም ሞተሀል የተባለ ሲሆን እንዲነቃና ንስሐ እንዲገባ አግዚአብሐየር አዟል። እንዲህ ካላደረገ ግን እንደሚፈርድበት "እመጣብሃለሁ" ሲል ነግሮታል። የፊልድልፍያው መልአክ /ጠባቂ/ ግን በእግዚአብሔር ፊት የተወደደና ቅዱስ ነበርና እግዚአብሔር እንዲህ አለው "ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ በአንተ ፊት የተከፈተ በር

ሰጥቼአለሁ፤ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና ስሜንም አልካድህምና። እነሆ አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን እሰጥሃለሁ እነሆ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ" /ራእ.3፥ 8-9/።

ለቅዱሳን ስግደት አይገባም የሚሉ ምንኛ ያልታደሉ ናቸው? "የተከፈተ በር ሰጥቼሀለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም" የተባለላቸውን ቅዱሳንን የሚመሰገኑበትን የጸጋ በር ሊዘጉ የሚሮጡ ምንኛ ምስኪኖች ናቸው? "እነሆ አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር" የተባሉ ክርስቲያን ሳይሆኑ ክርስቲያን ነን የሚሉ ነገር ግን የሚዋሹ ምንኛ አሳዛኝ ናቸው? እነሆ ክርስቲያን ሳይሆኑ ክርስቲያን ነኝ በሚል ቅዠት ቅዱሳንን የማይወዱ የሰይጣን ማኅበር አባላት መባላቸው እንዴት የሚደንቅ ነው? እንደ ቅዱሳን ሁሉ እንዲ ሰጣቸው ተፈጥረው እነርሱ ራሳቸው ተላልፈው መሰጠታቸውና ባይወዱም እንኳን በቅዱሳን እግር ፊት መስገዳቸው የማይቀር መሆኑ እንዴት ግሩም ነው? በተዐብዮ ራሳቸውን እኔም እንደ እገሌ ቅዱስ ነኝ የሚሉ ዘባቾች ቅዱሳንን በትሕትናቸውና አንዱ ለአንዱ በመስገዳቸው የሚወድ

እግዚአብሔር “እንዴት እንደወደድሁህ ያውቁ

ዘንድ አደርጋቸዋለሁ” ብሎ ለቅዱሳን ቃል መግባቱ እንዴት

ያለ ምሥጢር ነው?

ወስብሀት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር!!!

በ ዲ/ን ሕሊና በለጠ ዘኖኅተብርሃን

@Micah Alaye

Yesterday at 1:39am · Public

· More

Milli Milli and 91 others like this.

View previous comments...

Alme Getachew

Amen amen amen kale how it yasemalen

Like · 1 · Reply · Report · Yesterday at 11:26am

Haymi Mengesha

Kale hiwot yasemalin

Like · 1 · Reply · Report · Yesterday at 2:20pm

Zewdnesh Mesfin

አሜን ቃለ ህይወትን ያሠማልን።

Like · 1 · Reply · Report · Yesterday at 4:56pm

Tensae Abay

Like · Reply · Report · Yesterday at 5:37pm

Tensae Abay

7/ ከመጽሀፍ ቅዱስ �ውስጥ ስእል ስለው አንተ ኢየሱስ ነህ ብለው ለስእሉ የሰገዱ እነማን ናቸው??

መላእክትን ወይም ድንግል ማርያምን ስእል ስለው የሰገዱ እነማን ናቸው ??

ስእል ስላችሁ ስገዱላቸው ያለው ማነው ??

ሳኦል ለሳሙኤል ሲሰግድ የት እንደነበር አላወቅክም ?

ልንገርህ :- ሳኦል የእግዚአብሄር መንፈስ ከእርሱ ተለይቶት እንደውም ክፉ መንፈስ ገብቶበት ነበር ከዚያም በአምላካችን ፊት ጸያፍ ወደሆነ ወደ ምዋርተኛ ሂዶ እያሚረተ ነበር ስለዚህ ለአንድ ክርስቲያን እንደ ሳኦል ያለ አመጸኛና ሟርተኛ መልካም ምሳሌ አይሆንም !!

ለሞተ የሚጸልይ እርሱም ሙት ነው !!

Like · Reply · Report · Yesterday at 5:49pm

6 replies

Micah Alaye

# Tensaye Abay

8/ «መጽሐፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል # አታውቁምና ትስታላችሁ» ማቴ 22÷29

እንዲል ምስጢርና ጥበብ የጎደላቸው መናፍቃን መጽሐፍትን አባታቸው ሉተር እንዳዘዛቸው እንደገዛ ፈቃድ እየተረጎሙ ጠፍተዋል ወደቀደመ ነገራችን አእንመለስና

እግዚአብሔር ስዕለ # መላእክትን ለሙሴ # እንዲሰራ አዘታልና ብዙዎች "የተቀረጸ ምስል ለአንተ አታድርግ ዘጸ 20፥4 የሚለውን በመያዝ አነስተኛ የመጽሃፍ ቅዱስ እውቀታቸውን በመጠቀም ይህ ጥቅስ ለታቦት ፣ለቅዱሳት ስእላት ፣እንዲሁም ለጌታ መስቀል እንደተጠቀሰ አድርገው የናገራሉ።

1.ይህ ጥቅስ ለታቦታት አለመጠቀሱን እንመልከት፥- ክብር ይግባውና እራሱ እግዚአብሄር “ታቦትን ስራ” በማለትሙሴን አዘታል ዘዳ 10፥1-5 እንግዲህ እግዚአብሄር የተቀረጸምስል ለአንተ አታድርግ ካለ በኋላ ታቦትን እንዲሰራ ማዘዙ ጣኦት አምልክ ማለቱነው? መልሱን ለእናንተ ልተው። ለማንኛውም

# ቅዱሳት_ስዕላት በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ የተሰሩ ስለመሆናቸው # ማስረጃው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፦=> በታቦተ ህጉ በጽላተ ኪዳኑ ላይ

# ስዕለ_ኪሩብ (ኪሩቤልን) እንዲስል እራሱ አምላካች # አእግዚአብሔር ሙሴን # አዝዞት ነበር => ዘፀ 25:19፣

ነገሥ ቀዳ 6:23 ፣

ሕዝ 9:3 10:1 ፣

ሔዋ 14:11

ዘፋ 3:24 ገላ. 3 ÷ 1 የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?" # ኢየሱስም የግብሩን፡ብር፡ አሳዩኝ፡አለ።እነር ሱም፡ዲናር፡አመጡለት። # ርሱም ፦ ይህች፡ # መልክ ፡ ጽሕፈቲቱስ፡ # የማን_ናት ፡አላቸው። # የቄሳር፡ነው፡አሉት።በዚያን፡ጊዜ፦

እንኪያስ፡የቄሳርን፡ለቄሳር፥ የእግዚአብሔርንም፥ ለእግዚአብሔር፡አስረክቡ፥ አላቸው። # ይህች_መልክ ሲል ለጊዜው የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ ሲል ለፍጻሜው ግን ይህች ስዕል ሲል # የቄሳርን_መልክ ለማለት ነው። ቄሳር ምንድን ነው? ሰው ነው ። ሰው የማን መልክ ነው? የእግዚአብሔር መልክ ነው። ታዲያ እግዚአብሔር ስዕለ ኪሩብን ስራ ማለቱ ጣኦትን ስራ መማለቱ ነውን???????????? ሎቱ ስብሀት

ይህ መናፍቃን ምን ያህል ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደራቁ የሚያሳይ ነው።

Berihuley Hadgu

9/ ለመላዕክት የፀጋ ስግደት ይገባል

1 ዜና 21÷16፤

ዳዊትም ዓይኖቹን አነሣ፤ የእግዚአብሔር መልአክ በምድርና በሰማይ መካከል ቆሞ፥ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ተዘርግቶ አየ። ዳዊትም ሽማግሌዎችም ማቅ ለብሰው በግምባራቸው ተደፉ።

"ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር። ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ ፊቱንም ደፍቶ ወደ

ምድር ሰገደ።" /ዘፍ 19÷1 /

ቃሉ ላይ ለማመጽና በማስተዋላችሁና በትዕቢት ላይ ለመመካት ያስመረጣችሁ እንዴት ያለ ክፉ መንፈስ ነው። ትዕቢት የማን ባህሪ ናት ? ትዕቢተኛስ ማነው? እንግዲህስ ልትነቅፉት የምትወዱት ማንን ነው? ሎጥን ወይንስ ሁለቱን መላእክት? ወይንስ እግዚአብሔርን ?

"እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ የእግዚአብሔርን መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ ሰገደም በግምባሩም ወደቀ።"

/ዘኍ 22 ÷31 /

የበለዓም የታወሩ አይኖችን አግዚአብሔር እስኪከፍታቸው ድረስ መልአኩን ማየት አልተቻለውም። አይኖቹ እስኪከፈት ድረስ በማስተዋል አህያው ትበልጠው ነበር። ማየት ያልቻለ ውሳጤያዊ አይኑን እግዚአብሔር በቸርነቱ ባበራለት ግዜ ግን ብርሃናዊውን ግሩም የእግዚአብሔርን መልአክ ከፊቱ ተመለከተው። ያኔ ለመልአኩ የጸጋ ስግደትን ሰገደ። አሁንስ ማንን ትከሳላችሁ? የዕውሩን አይኖች አብርቶ መልአኩን እንዲመለከትና የአክብሮት ስግደት ይሰግድ ዘንድ የፈቀደለትን እግዚአብሔርን? ወይስ የጸጋ ስግደት ሲቀርብለት ሳይቃወም የተገባውን አክብሮት የተቀበለውን ቅዱሱን መልአክ? ወይንስ ከእውርነትና ከቁጣ መንፈስ ተመልሶ ትህትናን በእግዚአብሔር ፊት የፈጸመውን በልአምን? ወይንስ ዘኁልቅን እንሰርዘው? ወይስ የተረት መጽሐፍ እንበለው? በእናንተ ዘንድ አህያ እንደተናገረች የሚናገር መጽሐፍ እንደምን ቅዱስ ተባለ? ከማስተዋላችሁና ከጥበባችሁስ የተነሳ ይህንን የደብተራውን የሙሴን መጽሐፍ እንደምን ተቀበላችሁት?

ይህስ ቃል ከሮሜ ምዕራፍ ስምንት ከሰላሳ አራተኛዋ ቁጥር ጋር እንደምን ቅዱስ ተባለ?

መሣፍንት 13÷20፤

ነበልባሉም ከመሠዊያው ላይ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ የእግዚአብሔርም መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ዐረገ፤ ማኑሄና ሚስቱም ተመለከቱ፥ በምድርም በግምባራቸው ተደፉ።

"እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድነው? አለው።" /ኢያ 5÷13 /

ፀሀይን በገባዖን ያቆመው አባታችን ኢያሱ በማስተዋል ጠየቀ። "እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን። የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ።" ብሎ በቅንአት አሰምቶ የተናገረ ኢያሱ ግን ለሰራዊት አለቃ ለቅዱሱ መልአክ የጸጋ ስግደትን ሰገደ። የትህትናና የፍቅርንም ስራ ሰራ። መናፍቃን ሆይ ኢያሱ ለጣኦት እየሰገደ ይሆን? ወይንስ "ከኔ በቀር አማልክት አይሁንላችሁ ለማንም አትስገዱ አትገዙ።" ያለውን አምላካዊ ትዕዛዝ እየሻረ ይሆን? ወይንስ የመላእክት አለቃ ሃያሉ መልአክ ለባለ ራዕዩ ዮሀንስ ከተገለጠው መልአክ ተለይቶ ያልተፈቀደ ስግደትን የሚፈቅድና በዝምታ የሚያልፍ ይሆን? እባካችሁ ወገኖች ቃሉን ማሸነፍ ከፍጥረታት ወገን ለማንም የሚቻል አይደለም።

መልአኩ ግን የጸጋ ሰጊድ እንጂ የአምልኮ ሰጊድአለመሆኑን ስላወቀ ጫማህን አውልቅ ብሎ በክብር ላይ ክብር ከመጨመር በቀር ለምህን ለኔ ትሰግዳለህ? እንዳታደርገው ተጠንቀቅ የሚልን ቃል ከቶ አልተናገረም።

ወይንስ መጽሐፈ ኢያሱንም እንቀንሰው ?

ራእይ 19÷10፤

ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ። እርሱም፦ እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነውና፥ አለኝ።

የመናፍቃን ትልቅ የመከራከሪያ ሐሳብ ቢኖር ይህ ነው።

ይህን ቅዱስ ቃል በመጥቀስ ለመላዕክት መስገድ አይገባም ይላሉ፣ እውነቱና ቀጥተኛ ትርጉሙ ደግሞ እነሱ እንደሚሉት አይደለም።

ዳሩ ግን የመላኩን አባባል ካለመረዳት እንጂ ለመላዕክት መስገድ ከሐይማኖት ውጭ ሁኖ ዩሐንስ ባለማወቅ የሰገደለት ሆኖ አይደለም ይህንንማ እንዳንል የሰጋጁ ዩሐንስ ማንነት ያግደናል።

ዩሐንስ ድንግላዊና የጌታ ሐዋሪያ ከመሆኑም ሌላ ጌታ የሚወደው፣ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ወንጌልን መልዕክክታትን የፃፈ፣ እንዲሁም የአለምን ፍፃሜ በራዕይ ያየ ነው።

ይህን ያህል የጌታ ባለሟል የሆነ ቅዱስን ሰው ስለትንሿ ነገር ለመላዕክት መስገድ ተገቢ አለመሆን አጥቶት በስህተት ሰገደ ማለት የፃፋቸው

ወንጌሎችም፣

መልዕክታትም

ስህተት አለባቸው እእንደማለት ነው።

ይህ ማለት ግን ሰው እእንደ እግዚአብሔር ፍፁም ነው ማለት አይደለም።

እሱ በፍፁም እምነት ውስጥ ሳይሆን፣ እሱ ማን መመለክ እንዳለበት

ሳያውቅ ለኛ ማሳወቅ አይችልምና።

ስለዚህ በስህተት ሰገደ ማለት ትልቅ ስህተት ነው።

ዩሐንስ ለመላኩ የአክብሮት ስግደት ያቀረበው ለመላዕክት መስገድ ተገቢ መሆኑን ስላወቀ ነው።

መልአኩ ደግሞ አትስገድልኝ ማለቱ የዩሐንስን ክብርና ማዕረግ መግለጡ ነው።

ዩሐንስ በክብሩ ከመልአኩ እኩል ሆኖ ነበርና ስግደት ደግሞ የበላይና የበታች መግለጫ ስለሆነ አንተኮ በክብር ከእኔ እኩል ነህ፣ ስለዚህ ለኔ አትስገድ አይገባም ቢለውም ዩሐንስ ግን ከመስገድ ወደኋላ አላለም።

ትሁት ነውና ይህንንም ለማረጋገጥ ከፊለግን ራዕ 22 ከቁጥር 7 ጀምረን እንመልከት።

እንግዲህ ዩሐንስ ተሳስቶ ሰገደ ቢባል እንኳን ሁለት ጊዜ ይሳሳታል ???

እውነት ግን መናፍቃን ወንድም እህቶቻችን ምን ያህል ቢታወሩ ነው ይህን ባለራዕይ በነሱ ከዜሮ በታች እውቀት ሊመዝኑት የተነሱት ???

የሆነው ሁኖ በሶስት ተከታታይ ክፍል ለቅዱሳን ሰወችና ለመላዕክታን እንዴት እንደሚሰገድ ቅዱስ መፅሐፍን ሚዛን አድርገን ተመልክተናል።

አሁን ደግሞ ለቤተክርስቲያንስ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያክል ጥቂቱን መረጃ ብቻ እንመልከት =>

ታቦት የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያድርበትና ስመ እግዚአብሔር የተፃፈበት ስለሆነ ሊከበርና ሊሰገድለትም ይገባል።

ፊልጵስዩስ 2÷10፤ " ጉልበት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከክ " ብሏልና።

ዘጸአት 33÷10፤

ሕዝቡም ሁሉ የደመናው ዓምድ በድንኳኑ ደጃፍ ሲቆም ያየው ነበር፤ ሕዝቡም ሁሉ ተነሥቶ እያንዳንዱ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግድ ነበር።

መዝሙር 132÷7፤

ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፤ እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን።

8፤ አቤቱ፥ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ፥ አንተና የመቅደስህ ታቦት።

ኢያሱ 7÷6፤

ኢያሱም ልብሱን ቀደደ፥ እርሱና የእስራኤልም ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድረስ በግምባራቸው ተደፉ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ።

እንዲህና መሰል ብዙ ተመሳሳይ መረጃወችንና ማስረጃወችን ከቅዱስ መፀሐፍ እያወጡ ማሳየት ቢቻልም ላስተዋለ ግን ይቺ ትንሽ ፅሁፍ ከበቂ በላይ ናት።

"እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ፥ እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት፣ መናገር እንኳ ነውር ነውና፤ ሁሉ ግን በብርሃን ሲገለጥ ይታያልና የሚታየው ሁሉ በብርሃን ነውና።" / ኤፌ 5÷1 /

በሐሰት ውንጀላ የጠፉ ወገኖችን ልዑል እግዚአብሔር ወደ ትክክለኛው በረት ይመልስልን ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ ከሁላችንም ጋር ይሁን አሜን::